የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፺፫
አዲስ አበባ ጥቅምት ፳፬ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

17th Year No. 93
ADDIS ABABA 4th November, 2011

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፯፻፲፮/፪ሺ፫ ዓ.ም

የኦዞን ንጣፍን የሚያሳሱ ኬሚካሎችን ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ .........ገጽ ፮ሺ፩፻፹፯

CONTENTS

Proclamation No. 716/2011

Control of Ozone Layer Depleting Substances Proclamation.... Page 6187

## አዋጅ ቁጥር ፯፻፲፮/፪ሺ፫

## የኦዞን ንጣፍን የሚያሳሱ ኬሚካሎችን ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ

ኢትዮጵያ የኦዞንን ንጣፍ የሚያሳሱ ኬሚካሎችን የሚመለከተውን የሞንትሪያል ፕሮቶኮልና ማሻሻያዎቹን ተቀብላ ያፀደቀች በመሆኑ፤

የሞንትሪያል ፕሮቶኮል እያንዳንዱ ፈራሚ አባል ሀገር በፕሮቶኮሉ አባሪዎች የተዘረዘሩትን ቁጥጥር የሚደረግባቸውን ንጥረ ነገሮች ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባትና ከሀገር ለማስወጣት የሚያስችል የፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት እንዲኖረው የሚጠይቅ በመሆኑ፤

ይህንኑ የፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት ለመዘርጋት የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ እንዲኖር የማድረግ አስፈላጊነቱ የታመነበት በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭/፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የኦዞን ንጣፍን የሚያሳሱ ኬሚካሎችን ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር ፯፻፲፮/፪ሺ፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION No. 716/2011.

## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE CONTROLING OF OZONE LAYER DEPLETING SUBSTANCES

WHEREAS. Ethiopia has ratified the Montreal Protocol on Substances that Deplete the Ozone Layer and its amendments thereto;

WHEREAS, the Montreal Protocol requires each party to the Protocol to establish a system for licensing the import and export of controlled substances listed in Annexes to the Protocol;

WHEREAS, it is deemed necessary to put in place a regulatory framework to implement same;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Control of Ozone Layer Depleting Substances Proclamation No. 716/2011."

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 5.80

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

፩/ "ባለሥልጣን" ማለት የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ነው፤

፪/ "መሣሪያ" ማለት የኦዞን ንጣፍን የሚያሳሳ ኬሚካል የሚጠቀም ወይም የሚያመነጭ ቴክኖሎጂ ወይም መሣሪያ ነው፤

፫/ "ነጋዴ" ማለት ማንኛውም የኦዞን ንጣፍን የሚያሳሱ ኬሚካሎችን ወይም መሣሪያዎችን በማስመጣት ወይም በመሸጥ ወይም መሣሪያዎችን በማደስ ወይም በመጠገን የንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ሰው ነው፤

፬/ "ፈቃድ ሰጪ አካል" ማለት የንግድ ፈቃድ ለመስጠት ወይም ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎችን ሕጋዊነት ለመቆጣጠር በሕግ ሥልጣን የተሰጠው ማንኛውም የፌዴራል ወይም የክልል መንግሥት አካል ነው፤

፭/ "የኦዞን ንጣፍ" ማለት ስትራቶስፌር በመባል በሚታወቀው ከባቢ አየር ውስጥ የሚገኝ የኦዞን ክምችት ነው፤

፮/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯ /፩/ የተጠቀሰው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችንም ይጨምራል፤

፯/ "የኦዞን ንጣፍን የሚያሳሱ ኬሚካሎች" ማለት ሳይደባለቁም ሆነ ተደባልቀው ጥቅም ላይ ሲውሉ የኦዞን ንጣፍን የሚያሳሱ ከዚህ አዋጅ ጋር ተያይዞ በሚገኘው ሠንጠረዥ የተዘረዘሩ ኬሚካሎች ናቸው፤

፰/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፱/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴት ንም ይጨምራል።

## የኦዞን ንጣፍን የሚያሳሱ ኬሚካሎችን ወደ ሀገር ውስጥ ስለማስገባት

፩/ ማንኛውንም የኦዞን ንጣፍን የሚያሳሳ ኬሚካል ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተው የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት የተከለከለ ነው።

## 2. Definitions

In this Proclamation, unless the context otherwise requires:

1/ "Authority" means the Environmental Protection Authority;

2/ "Appliance" means technology or equipment that employ or emit substances that deplete the ozone layer;

3/ "Dealer" means any person engaged in the importation or selling of ozone layer depleting substances or appliances or the maintenance or repair of appliances;

4/ "Licensing Authority" means any federal or regional government organ empowered by law to issue business license or to control imports;

5/ "Ozone Layer" means the layer of atmospheric ozone within the stratosphere;

6/ "Region" means any region referred to in Article 47(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa and Dire Dawa city administrations;

7/ "Ozone Depleting Substances" means ozone-depleting substances, whether existing alone or in mixture, listed in the schedule attached hereto;

8/ "Person" means a natural or juridical person;

9/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

## 3. Importation of Ozone Depleting Substances

1/ The importation of any ozone-depleting substance is prohibited after the laps of the phase-out date stated in the schedule attached to this Proclamation.

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ድንጋጌ ቢኖርም የኬሚካል ግዥው የተፈፀመው ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት ስለመሆኑ ወይም ኬሚካሉ የተፈለገው የአገልግሎት ጊዜው ያላለፈ መሣሪያን ለማንቀሳቀሻ፣ ለማደሻ ወይም ለመጠገኛ ስለመሆኑ አሳማኝ ማስረጃ ከቀረበ ባለሥልጣኑ ክልከላውን ሊያነሳ ይችላል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪/ መሠረት ክልከላው እንዲነሳለት የሚፈልግ ነጋዴ ተገቢውን ፎርም በመሙላት ለባለሥልጣኑ ማመልከት አለበት።

፬/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፫/ መሠረት የቀረበለትን ጥያቄ ያልተቀበለበትን ሆነ የተቀበለበትን ምክንያት ለአመልካቹ በጽሑፍ ያሳውቃል።

፬. <u>መሣሪያዎችን ወደ ሀገር ውስጥ ስለማስገባት</u>

፩/ የኦዞን ንጣፍን የሚያሳሳ ኬሚካል የሚጠቀም ወይም የሚያመነጭ መሣሪያ ወይም ቴክኖ ሎጂ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት የተከለከለ ነው።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ድንጋጌ ቢኖርም ግዥው የተፈፀመው ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት ስለመሆኑ ወይም አማራጭ መሣሪያ ወይም ቴክኖሎጂ የሌለ ስለመሆኑ አሳማኝ ማስረጃ ከቀረበ ባለሥልጣኑ ክልከላውን ሊያነሳ ይችላል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪/ መሠረት ክልከላው እንዲነሳለት የሚፈልግ ነጋዴ ተገቢውን ፎርም በመሙላት ለባለሥልጣኑ ማመልከት አለበት።

፬/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፫/ መሠረት የቀረበለትን ጥያቄ ያልተቀበለበትን ሆነ የተቀበለበትን ምክንያት ለአመልካቹ በጽሑፍ ያሳውቃል።

፭. <u>መሣሪያዎችን ስለመጠገን እና ስለማደስ</u>

መሣሪያዎች ሲጠገኑና ሲታደሱ የኦዞንን ንጣፍ የሚያሳሱ ኬሚካሎች በማያመነጩበት መንገድ መሆን ይኖርበታል።

2/ Notwithstanding the provision of sub-article (1) of this Article, the Authority may waive the prohibition where a reliable evidence is submitted to prove that the transaction has been initiated prior to the coming into force of this Proclamation or the substance is needed to run, repair or service an appliance that has not yet outlived its useful life.

3/ A dealer requiring a waiver pursuant to sub-article (2) of this Article shall apply, in the prescribed form, to the Authority.

4/ The Authority shall inform the applicant, in writing, of the reasons for the rejection or acceptance of the application submitted to it pursuant to sub-article (3) of this Article.

4. <u>Importation of Appliances</u>

1/ The importation of appliance or technology that employs or emits ozone depleting substances is prohibited.

2/ Notwithstanding the provision of sub-article (1) of this Article, the Authority may waive the prohibition where a reliable evidence is submitted to prove that the transaction has been initiated prior to the coming into force of this Proclamation or no alternative appliance or technology is available.

3/ A dealer requiring a waiver pursuant to sub-article (2) of this Article shall apply, in the prescribed form, to the Authority.

4/ The Authority shall inform the applicant, in writing, of the reasons for the rejection or acceptance of the application submitted to it pursuant to sub-article (3) of this Article.

5. <u>Repairing and Servicing of Appliances</u>

Repairing and servicing of appliances shall be undertaken in a manner that arrests the emission of ozone depleting substances.

## ፮. ድርጅቶችን ስለማቋቋም ፣ ማካሄድና ማስፋፋት

፩/ ማንኛውም ሰው ከባለሥልጣኑ የተሰጠ ፈቃድ ሳይኖረው የኦዞንን ንጣፍ የሚያሳሱ ኬሚካ ሎችን አጠቃቀም ሊያሳድግ የሚችል አሠራር የሚኖረው ድርጅት ማቋቋም፣ ማካሄድ ወይም ማስፋፋት አይችልም።

፪/ የኦዞን ንጣፍን የሚያሳሱ ኬሚካሎችን አጠቃቀም ሊያሳድግ የሚችል አሠራር የሚኖረው ድርጅትን ለማቋቋም፣ ለማካሄድ ወይም ለማስፋፋት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በተገቢው ፎርም ለባለሥልጣኑ ማመልከት አለበት።

፫/ ባለሥልጣኑ የፈቃድ መጠየቂያ ማመልከቻውን እንደተቀበለ ማመልከቻውን መርምሮ ፈቃዱን በመከልከል ወይም ቅድመ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ወይም ያልተመሰረተ ፈቃድ በመስጠት መወሰን አለበት።

፬/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፫/ መሠረት የቀረበለትን ጥያቄ ያልተቀበለው እን ደሆነ ያልተቀበለበትን ምክንያት ለአመልካቹ በጽሑፍ ያሳውቃል።

## ፯. ስለፈቃድ ዕድሳት

በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠ ፈቃድ ካልታደሰ በቀር የሚያገለግለው ለአንድ ዓመት ብቻ ይሆናል።

## ፰. ፈቃድን ስለማገድና መሰረዝ

፩/ ማንኛውም ሰው በተሰጠው ፈቃድ የተቀመጡ ገደቦችንና ሁኔታዎችን ለመተላለፉ አሳማኝ ምክንያት ሲገኝ ወይም ለሕብረተሰቡ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠን ፈቃድ ሊያግድ ወይም ሊሰርዝ ይችላል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት ፈቃዱ የታገደበት ወይም የተሰረዘበት ማንኛውም ሰው ስለፈቃዱ መታገድ ወይም መሰረዝ ማስታወቂያ በደረሰው በ፲፭ የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን በጽ ሑፍ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ ይችላል። ባለሥል ጣኑም የቀረበለትን ቅሬታ መርምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የመጨረሻ ውሳኔ መስጠት አለበት።

፫/ ባለሥልጣኑ ቅሬታውን መርምሮ የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት የተሰጠ የፈቃድ ዕገዳ ወይም የፈቃድ መሠረዝ አይነሳም።

## 6. Establishing, Running or Expanding Enterprises

1/ Without having authorization from the Authority, no person may establish, run or expand an enterprise with operations likely to increase the consumption of ozone depleting substances.

2/ Any person desirous of establishing, operating or expanding an enterprise with operations likely to increase the consumption of ozone depleting substances shall apply, in the prescribed form, to the Authority.

3/ The Authority, upon receipt of such application, shall review the application and give a decision either refusing or granting authorization with or without conditions.

4/ Where the Authority rejects the application submitted to it pursuant to sub-article (3) of this Article, it shall inform the applicant, in writing, of the reasons for the rejection of the application.

## 7. Renewal of Authorization

Authorization issued pursuant to this Proclamation shall, unless renewed, be valid only for one year.

## 8. Suspension and Cancelation of Authorization

1/ Where there is sufficient reason to believe that any person has committed a breach of the terms and conditions of authorization, or that public interest requires to do so, the Authority may suspend or cancel any authorization granted pursuant to this Proclamation.

2/ Any person, whose authorization has been suspended or cancelled in accordance with sub-article (1) of this Article, may submit written complaint to the Authority with in 15 working days from the date of receiving such notification; and the Authority shall give a final decision within one month from the date of receipt of such a complaint.

3/ Until a final decision is issued by the Authority, there shall be no stay of execution of the cancellation or suspension made pursuant to sub-article (1) of this Article.

፱. የነጋዴዎች ግዴታ

፩/ ማንኛውም ነጋዴ ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባቸውን፣ የሸጣቸውን፣ የጠገናቸውን፣ ያደሳቸውን ወይም ያመረታቸውን መጠን፣ ዓይነት እንዲሁም የተሰሩበትን ሀገር የሚመዘግብበት መዝገብ መያዝ እና በየጊዜው ለባለሥልጣኑ ሪፖርት የማድረግ ግዴታ አለበት።

፪/ ማንኛውም ነጋዴ አግባብነት ያለውን የምርቱን አጠቃቀም መመሪያ በመጠቀም በሚሸጣቸው የኦዞን ንጣፍን የሚያሳሱ ኬሚካሎች ወይም መሣሪያዎች ላይ ተገቢውን መለያ በማድረግ ማስተዋወቅ አለበት።

፫/ ማንኛውም ነጋዴ በፈቃዱ የተመለከቱ አስገዳጅ ሁኔታዎችን የማክበርና የመተግበር ግዴታ አለበት።

፲. የፈቃድ ሰጪ አካል ግዴታ

ፈቃድ ሰጪ አካላት በባለሥልጣኑ የተሰጠ ፈቃድ የመከልከል፣ የመስጠት፣ የማገድ ወይም የመሰረዝ ውሳኔን በመከተል በተመሳሳይ የንግድ ፈቃድ የመከልከል፣ የመስጠት፣ የማገድ ወይም የመሰረዝ ኃላፊነታቸውን መወጣት አለባቸው።

፲፩. የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር

በሞንትሪያል ፕሮቶኮል ላይ የተደረጉ ማሻሻያዎች ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፮/፪ሺ፩ አንቀጽ ፫ ድንጋጌ ቢኖርም ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ ኬሚካሎችና መሣሪያዎች ጊዜያቸውን ጠብቀው ቀስ በቀስ ከገበያ የሚወጡበትን የጊዜ ሰሌዳ የማቀድና ዝርዝራቸውንም የማተም፤

፪/ ፈቃድ የመስጠት፣ የማደስ፣ የማገድ ወይም የመሰረዝ እንዲሁም የጥገና አገልግሎት ሰጪዎችን፣ የአምራቾችን፣ የአቅራቢዎችን፣ የአስመጪዎችንና ላኪዎችን ስምና አድራሻ መዝገቦ የመያዝ፤

፫/ በዘርፉ መደበኛ ባልሆነ መልኩ ከጥገናና ከዕድሳት ጋር በተያያዘ ለተሰማሩ ክፍሎች ሕጉን ለመከተል የሚያስችላቸውን መንገድ የመቀየስ፣ የማስተዋወቅና የመተግበር፤

፬/ የኦዞን ንጣፍን የማያሳሱ አማራጭ ኬሚካሎች፣ ልምዶችና ቴክኒኮች እንዲስፋፉ በህዝብ ዘንድ የግንዛቤ ማስጨበጫና የሥልጠና ፕሮግራሞች ለመስጠት እንዲሁም የቴክኒክና ገንዘብ ድጋፍ ለማድረግ የሚያስችል ሀብት የማፈላለግ፤

9. Duty of Dealers

1/ All dealers shall maintain a register to record the quantity, the type and the country of origin of ozone depleting substances and appliances imported, sold, repaired, serviced or manufactured, as the case may be, and provide the Authority with such information periodically.

2/ Any dealer shall, in accordance with the relevant guidelines of the product, label and publicize ozone depleting substances or appliances he is trading in.

3/ Any dealer shall comply with the terms and conditions of authorization.

10. Duty of Licensing Authority

Licensing authorities shall refuse, grant, renew, suspend or cancel trade licenses in tandem with the decision of the Authority to refuse, grant, renew, suspend or cancel authorization.

11. Powers and Duties of the Authority

Notwithstanding the provisions of Article 3 of Montreal Protocol Amendments Ratification Proclamation No.656/2009, the Authority shall have the powers and duties to:

1/ formulate a periodic phasing out schedule and publish list of appliances and substances;

2/ grant, renew, suspend or cancel authorizations and maintain a register, which shall contain the names and addresses of repairers, manufacturers, suppliers, importers and exporters;

3/ design, promote and implement a mechanism that would enhance the compliance of the informal sector in connection with repairing and servicing of appliances;

4/ solicit resources in order to undertake public awareness and training programs as well as provide technical and financial support that would foster the use of alternative substances, practices and techniques;

፭/ ይህን አዋጅ የሚፃረር ተግባር ተፈጽሟል ወይም እየተፈፀመ ነው ብሎ ሲያምን ወደማንኛውም ቅጥር ግቢ በመግባት ማንኛውንም መሣሪያ ወይም ንጥረ ነገር የመመርመር እንዲሁም ለምርመራ የንጥረ ነገር ናሙና የመውሰድ፤

፮/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለሌሎች የፌዴራል ወይም የክልል መንግሥት አካላት የሥልጣን ውክልና የመስጠት፤

፯/ ስለዚህ አዋጅ አፈጻጸም አግባብነት ላላቸው አካላት ሪፖርት የማቅረብ፤

፰/ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባራትን የማከናወን።

## ፲፪. ቅ ጣ ት

፩/ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ድንጋጌዎች እንደተ ጠበቁ ሆኖ ይህን አዋጅ ወይም ሌላ አግባብ ያለውን ህግ የሚተላለፍ ማንኛውም ሰው ጥፋት ፈጽሟልና ቅጣት ይጣልበታል።

፪/ ማንኛውንም የኦዞን ንጣፍን የሚያሳሳ ኬሚካል ወደ ሀገር ውስጥ ከመግባቱ በፊት በባለሥልጣኑ ወይም ከሚመለከተው የክልል የአካባቢ ጥበቃ መሥሪያ ቤት ይሁንታ ሳያገኝ ተግባራዊ ያደረገ እንደሆነ ጥፋት ፈፅሟልና ከ፲ሺ ብር /ከአስር ሺ ብር/ በማያንስ የገንዘብ መቀጮ ወይም እስከ ሁለት ዓመት በሚደርስ እሥራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል።

፫/ ማንኛውንም የኦዞን ንጣፍን የሚያሳሳ ኬሚካል የሚጠቀሙ መሣሪያዎች ሲጠገኑና ሲታደሱ ኬሚካሎች በማያመነጨበት መንገድ መሆን ይኖርበታል። ይህን ግዴታ ያልተወጣ ጥፋት ፈፅሟልና ከ፲ሺ ብር /ከአስር ሺ ብር/ በማያንስ የገንዘብ መቀጮ ወይም እስከ አንድ ዓመት በሚደርስ እሥራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል።

፬/ ማንኛውም የኦዞን ንጣፍን በሚያሳሳ የኬሚካል መሣሪያዎች ንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ነጋዴ ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባቸውን፣ የሸጣቸውን፣ የጠገናቸውን፣ ያደሳቸውን ወይም ያመረታቸውን መሳሪያዎች መጠን፣ አይነት እንዲሁም የተሰሩበትን ሀገር የሚመዘገብበት መዝገብ መያዝ እና በየጊዜው ለባለሥልጣኑ ሪፖርት የማድረግ ግዴታ አለበት። ይህን ግዴታ ካልተወጣ ጥፋት ፈፅሟልና ከ፲ሺ ብር /ከአስር ሺ ብር/ በማያንስና ከ፳ሺ ብር /ከሃያ ሺ ብር/ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

5/ enter any premise and inspect any appliance or substance where there is a reasonable ground to believe that an offence under this Proclamation have been or being committed and take samples of any substance for test;

6/ where necessary, delegate its powers and duties to other federal or regional government bodies;

7/ report on the implementation of this Proclamation to appropriate bodies;

8/ carry out such other activities as are necessary for the implementation of this Proclamation.

## 12. Penalty

1/ Without prejudice to the provisions of the Criminal Code, any person who violates the provision of this Proclamation or of any other relevant law commits an offence and shall be liable accordingly.

2/ Without obtaining authorization from the Authority or the relevant regional environmental agency importing of any ozone-depleting substance to the country, shall be punishable with fine not less than Birr 10,000 (ten thousand Birr) or imprisonment not exceeding two years, or with both.

3/ When repairing and servicing appliances containing ozone depleting substances it shall be undertaken in a manner that arrests the emission. Violation of this obligation is an offence punishable with fine not less than Birr 10,000 (ten thousand Birr) or imprisonment not exceeding one year, or with both.

4/ Any dealer engaged in ozone depleting substances or appliances business shall have the obligation to keep records of the quantity, the type and the country of origin of ozone depleting substances and appliances imported, sold, repaired, serviced or manufactured, and shall have the obligation to report same to the Authority from time to time. Violation of this obligation shall be punishable with a fine not less than Birr 10,000 (ten thousand Birr) and not exceeding birr 20,000 (twenty thousand Birr).

፭/ ይህን አዋጅ ወይም በአዋጁ መሠረት የሚወጣውን ማንኛውንም ደንብ ወይም መመሪያ በመጣስ ጥፋተ ኛነቱ የተረጋገጠ ሰው ከሚወሰንበት ከማንኛውም ቅጣት በተጨማሪ የደረሰውን ጉዳት በሙሉ በራሱ ወጪ እንዲያስተካክል ወይም እንዲተካ ፍርድ ቤቱ ማዘዝ ይችላል።

**፲፫. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስ ፈፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።

፪/ ባለሥልጣኑ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስ ፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

**፲፬. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

**፲፭. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥቅምት ፳፬ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት



5/ The court before which a person is prosecuted for an offence under this Proclamation or regulations or directives pursuant to this Proclamation may, in addition to any penalty it may impose, order the convicted person to restore or in any other way compensate for the damage inflicted.

**13. Power to Issue Regulation and Directive**

1/ The Council of Ministers may issue regulations necessary for the proper implementation of this Proclamation.

2/ The Authority may issue directives necessary for the implementation of this Proclamation and regulations issued pursuant to sub-article (1) of this Proclamation.

**14. Inapplicable laws**

No law shall, in so far as it is inconsistent with this Proclamation, be applicable with respect to matters provided for herein.

**15. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazeta

**Done at Addis Ababa, this 4th day of November, 2011**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

## ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | ቁጥጥር የሚደረግባቸው ኬሚ ካሎች ዝርዝር ምልክት | የጊዜ ገደብ /እንደ /አውሮፓውያን አቆጣጠር/ |
|---|---|---|
| ፩ | $CHFBr_2$ | ፲፱፻፺፮ |
| ፪ | $CHF_2Br$ | ፲፱፻፺፮ |
| ፫ | $CH_2 FBr$ | ፲፱፻፺፮ |
| ፬ | $C_2 HFBr_4$ | ፲፱፻፺፮ |
| ፭ | $C_2 HF_2 Br_3$ | ፲፱፻፺፮ |
| ፮ | $C_2 HF_3 Br_2$ | ፲፱፻፺፮ |
| ፯ | $C_2 HF_4 Br$ | ፲፱፻፺፮ |
| ፰ | $C_2 H_2 F_2 Br_2$ | ፲፱፻፺፮ |
| ፱ | $C_2 H_2 F_3 Br$ | ፲፱፻፺፮ |
| ፲ | $C_2 H_3 FBr_2$ | ፲፱፻፺፮ |
| ፲፩ | $C_2 H_3 F_2 Br$ | ፲፱፻፺፮ |
| ፲፪ | $C_2 H_4 FBr$ | ፲፱፻፺፮ |
| ፲፫ | $C_3 HFBr_6$ | ፲፱፻፺፮ |
| ፲፬ | $C_3 HF_2 Br_5$ | ፲፱፻፺፮ |
| ፲፭ | $C_3 HF_3 Br_4$ | ፲፱፻፺፮ |
| ፲፮ | $C_3 HF_4 Br_3$ | ፲፱፻፺፮ |
| ፲፯ | $C_3 HF_5 Br_2$ | ፲፱፻፺፮ |
| ፲፰ | $C_3 HF_6 Br$ | ፲፱፻፺፮ |
| ፲፱ | $C_3 H_2 FBr_5$ | ፲፱፻፺፮ |
| ፳ | $C_3 H_2 F_2 Br_4$ | ፲፱፻፺፮ |
| ፳፩ | $C_3 H_2 F_3 Br_3$ | ፲፱፻፺፮ |
| ፳፪ | $C_3 H_2 F_4 Br_2$ | ፲፱፻፺፮ |
| ፳፫ | $C_3 H_2 F_5 Br$ | ፲፱፻፺፮ |
| ፳፬ | $C_3 H_3 FBr_4$ | ፲፱፻፺፮ |
| ፳፭ | $C_3 H_3 F_2 Br_3$ | ፲፱፻፺፮ |
| ፳፮ | $C_3 H_3 F_3 Br_2$ | ፲፱፻፺፮ |
| ፳፯ | $C_3 H_3 F_4 Br$ | ፲፱፻፺፮ |
| ፳፰ | $C_3 H_4 FBr_3$ | ፲፱፻፺፮ |
| ፳፱ | $C_3 H_4 F_2 Br_2$ | ፲፱፻፺፮ |

## SCHEDULE

| No | List of Controlled Substances Symbol | Phase-out Date |
|---|---|---|
| 1 | $ChFBr_2$ | 1996 |
| 2 | $CHF_2Br$ | 1996 |
| 3 | $CH_2 FBr$ | 1996 |
| 4 | $C_2 HFBr_4$ | 1996 |
| 5 | $C_2 HF_2 Br_3$ | 1996 |
| 6 | $C_2 HF_3 Br_2$ | 1996 |
| 7 | $C_2 HF_4 Br$ | 1996 |
| 8 | $C_2 H_2 F_2 Br_2$ | 1996 |
| 9 | $C_2 H_2 F_3 Br$ | 1996 |
| 10 | $C_2 H_3 FBr_2$ | 1996 |
| 11 | $C_2 H_3 F_2 Br$ | 1996 |
| 12 | $C_2 H_4 FBr$ | 1996 |
| 13 | $C_3 HFBr_6$ | 1996 |
| 14 | $C_3 HF_2 Br_5$ | 1996 |
| 15 | $C_3 HF_3 Br_4$ | 1996 |
| 16 | $C_3 HF_4 Br_3$ | 1996 |
| 17 | $C_3 HF_5 Br_2$ | 1996 |
| 18 | $C_3 HF_6 Br$ | 1996 |
| 19 | $C_3 H_2 FBr_5$ | 1996 |
| 20 | $C_3 H_2 F_2 Br_4$ | 1996 |
| 21 | $C_3 H_2 F_3 Br_3$ | 1996 |
| 22 | $C_3 H_2 F_4 Br_2$ | 1996 |
| 23 | $C_3 H_2 F_5 Br$ | 1996 |
| 24 | $C_3 H_3 FBr_4$ | 1996 |
| 25 | $C_3 H_3 F_2 Br_3$ | 1996 |
| 26 | $C_3 H_3 F_3 Br_2$ | 1996 |
| 27 | $C_3 H_3 F_4 Br$ | 1996 |
| 28 | $C_3 H_4 FBr_3$ | 1996 |
| 29 | $C_3 H_4 F_2 Br_2$ | 1996 |

ቃ

# ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | ቁጥጥር የሚደረግባቸው ኬሚካሎች ዝርዝር ምልክት | የጊዜገደብ/እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር/ |
|---|---|---|
| ፶፰ | $C_2HFCl_4$ | ፪ሺ፴ |
| ፶፱ | $C_2HF_2Cl_3$ | ፪ሺ፴ |
| ፷ | $CHCl_2CF_3$ | ፪ሺ፴ |
| ፷፩ | $C_2HF_4Cl$ | ፪ሺ፴ |
| ፷፪ | $CHFClCF_3$ | ፪ሺ፴ |
| ፷፫ | $C_2H_2FCl_3$ | ፪ሺ፴ |
| ፷፬ | $C_2H_2F_2Cl_2$ | ፪ሺ፴ |
| ፷፭ | $C_2H_2F_3Cl$ | ፪ሺ፴ |
| ፷፮ | $C_2H_3FCl_2$ | ፪ሺ፴ |
| ፷፯ | $CH_3CFCl_2$ | ፪ሺ፴ |
| ፷፰ | $C_2H_3F_2Cl$ | ፪ሺ፴ |
| ፷፱ | $CH_3CF_2Cl$ | ፪ሺ፴ |
| ፸ | $C_2H_4FCl$ | ፪ሺ፴ |
| ፸፩ | $C_3HFCl_6$ | ፪ሺ፴ |
| ፸፪ | $C_3HF_2Cl_5$ | ፪ሺ፴ |
| ፸፫ | $C_3HF_3Cl_4$ | ፪ሺ፴ |
| ፸፬ | $C_3HF_4Cl_3$ | ፪ሺ፴ |
| ፸፭ | $C_3HF_5Cl_2$ | ፪ሺ፴ |
| ፸፮ | $CF_3CF_2CHCl_2$ | ፪ሺ፴ |
| ፸፯ | $CF_3ClCF_2CHClF$ | ፪ሺ፴ |
| ፸፰ | $C_3HF_6Cl$ | ፪ሺ፴ |
| ፸፱ | $C_3H_2FCl_5$ | ፪ሺ፴ |
| ፹ | $C_3H_2F_2Cl_4$ | ፪ሺ፴ |
| ፹፩ | $C_3H_2F_3Cl_3$ | ፪ሺ፴ |
| ፹፪ | $C_3H_2F_4Cl_2$ | ፪ሺ፴ |
| ፹፫ | $C_3H_2F_5Cl$ | ፪ሺ፴ |
| ፹፬ | $C_3H_3F_2Cl_3$ | ፪ሺ፴ |
| ፹፭ | $C_3H_3F_2Cl_3$ | ፪ሺ፴ |
| ፹፮ | $C_3H_3F_3Cl_2$ | ፪ሺ፴ |
| ፹፯ | $C_3H_3F_4Cl$ | ፪ሺ፴ |

# SCHEDULE

| No. | List of Controlled Substances Symbol | Phase-out Date |
|---|---|---|
| 58 | $C_2HFCl_4$ | 2030 |
| 59 | $C_2HF_2Cl_3$ | 2030 |
| 60 | $CHCl_2CF_3$ | 2030 |
| 61 | $C_2HF_4Cl$ | 2030 |
| 62 | $CHFClCF_3$ | 2030 |
| 63 | $C_2H_2FCl_3$ | 2030 |
| 64 | $C_2H_2F_2Cl_2$ | 2030 |
| 65 | $C_2H_2F_3Cl$ | 2030 |
| 66 | $C_2H_3FCl_2$ | 2030 |
| 67 | $CH_3CFCl_2$ | 2030 |
| 68 | $C_2H_3F_2Cl$ | 2030 |
| 69 | $CH_3CF_2Cl$ | 2030 |
| 70 | $C_2H_4FCl$ | 2030 |
| 71 | $C_3HFCl_6$ | 2030 |
| 72 | $C_3HF_2Cl_5$ | 2030 |
| 73 | $C_3HF_3Cl_4$ | 2030 |
| 74 | $C_3HF_4Cl_3$ | 2030 |
| 75 | $C_3HF_5Cl_2$ | 2030 |
| 76 | $CF_3CF_2CHCl_2$ | 2030 |
| 77 | $CF_3ClCF_2CHClF$ | 2030 |
| 78 | $C_3HF_6Cl$ | 2030 |
| 79 | $C_3H_2FCl_5$ | 2030 |
| 80 | $C_3H_2F_2Cl_4$ | 2030 |
| 81 | $C_3H_2F_3Cl_3$ | 2030 |
| 82 | $C_3H_2F_4Cl_2$ | 2030 |
| 83 | $C_3H_2F_5Cl$ | 2030 |
| 84 | $C_3H_3F_2Cl_3$ | 2030 |
| 85 | $C_3H_3F_2Cl_3$ | 2030 |
| 86 | $C_3H_3F_3Cl_2$ | 2030 |
| 87 | $C_3H_3F_4Cl$ | 2030 |

## ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | ቁጥጥር የሚደረግባቸው ኬሚካሎች ዝርዝር ምልክት | የጊዜገደብ/እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር/ |
|---|---|---|
| ፹፰ | $C_3H_4FCI_3$ | ፪ሺ፴ |
| ፹፱ | $C_3H_4F_2CI_2$ | ፪ሺ፴ |
| ፺ | $C_3H_4F_3CI$ | ፪ሺ፴ |
| ፺፩ | $C_3H_5FCI_2$ | ፪ሺ፴ |
| ፺፪ | $C_3H_5F_2CI$ | ፪ሺ፴ |
| ፺፫ | $C_3H_6FCI$ | ፪ሺ፴ |

## SCHEDULE

| No. | List of Controlled Substances Symbol | Phase-out Date |
|---|---|---|
| 88 | $C_3H_4FCI_3$ | 2030 |
| 89 | $C_3H_4F_2CI_2$ | 2030 |
| 90 | $C_3H_4F_3CI$ | 2030 |
| 91 | $C_3H_5FCI_2$ | 2030 |
| 92 | $C_3H_5F_2CI$ | 2030 |
| 93 | $C_3H_6FCI$ | 2030 |